**መልዕክት ከአሲምባዎች፦**

**በምዕራቡ ዓለም መብታችን ተጠብቆ የምንኖር ኢትዮጵያውያን በሌላው ዓለም ወገኖቻችን እንዴት እንደሚኖሩ የሚከተለውን መጣጥፍ አንብበን ምን ማድረግ እንዳለብን በያለንበት እንምከርና ባፋጣኝ እንድረስላቸው !**

## በ UNHCR ስራ ሞት ይደንግጥ....የመን ያለ ስደተኛ መደንገጥ ትቷል

ከግሩም ተክለሃይማኖት

ረሀብ ... እርዛት ... መንሳቆል ... ፍርሃት ... የጎዳውን ስደተኛ አስለቃሽ ጭስ መጠቀም ... በጥይት ማቁሰል ... በዱላ መደብደብ ከ UNHCR የተሰጠ መፍትሄ ነው:: እሁድ የመን ላለን ስደተኞች የተረገመ ቀን ነው



የሆነው:: የመን በጦርነት ውስጥ መዳከር ከጀመረች ጀምሮ በኢትዮጵያዊያን እና ኤርትራዊያን ላይ እየደረሰ ላለው ችግር፣ አሳባ ከሚባለው አካባቢ የተፈናቀሉትን ጨምረን መፍትሄ ስጡን ብለን UNHCR በር ላይ ከወደቅን 32 ቀናችን ነው:: በዚህ ጉዳይ እና የመን ያለችበትን ሁኔታ ለማጣራት ከውጭ የመጡ የልዑካን ቡድን በ UNHCR ቢሮ መገኘታቸውን ሰማን:: ልናናግራቸው፣ ችግራችንን ልናሳውቃቸው መፈለጋችንን በስነ-ስርዓት ጠየቅን:: እንግዶቹን እንዳናገኛቸው አድርገው በሌላ በር ካስወጡ በኋላ አድማ በታኝ ፖሊስ ያመጡት የ UNHCR ቢሮ ሰራተኞች ወተው "ተነሱ ያለበለዚያ በሀይል ያስነሷችኋል" አሉን::



"እንነሳም መፍትሄ ነው የምንፈልገው" አልን:: ደበደቡን ... በጥይት መቱን ... በአስለቃሽ ጋዝ ... ራስን በሚያስት ኬሚካል አጠኑን:: ከመቶ ሰው በላይ ተጎድቷል:: በጥይት ጉዳት የደረሰባቸው አህመድ ... ስለሺ ...ቀለል ያል ጉዳት ሲደርስባቸው ኡስማን አብዳ ከዚህ በፊት ሚስቱ UNHCR በር ላይ በፖሊስ ተደብድባ የ 5 ወር ጽንስ ያስወረደች አሁን እሱ ደሞ አንገቱ ላይ በጥይት ተመታ:: ሰለሞን እና አሁን ስሙን ያላስታወስኩት ልጅ እግራቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው:: በዱላ እና ራስን በመሳት ችግር የገጠማቸው ከ 100 በላይ ናቸው:: በዛን ሰዓት በልብ ችግር ምክንያት ታምሜ የተነሳሁበት ወቅት ነበር:: የመተንፈስ ችግር ስላልብኝ አስለቃሽ ጋዙም ሆነ ራስ እንዲስቱ የሚያደርገው ኬሚካል ተደማምረው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ስለነበርኩ ለህክምና የወሰዱኝ ቦታ ምን ያህል እንደቆየሁ ሲነግሩኝ አዘንኩ:: እውን በስደተኛ ላይ የሚወሰድ እርምጃ ነው UNHCR የወሰደው? የቢሮው መቋቋምስ አላማው ስደተኞችን ማገልገል ነው ወይስ ገንዘብ እየከፈሉ ማስደብደብ ነው?ማስደብደቢያ የከፈሉት ለስንት ደሃ ስደተኛ የአመት ቀለብ ይሆን ነበር?

በዛ ላይ አለም አቀፍ ተቋምነቱ ሀገርን ከሀገር ለማጋጨት፡ ብሄርን ከብሄር ለማጋጨት የሚጠቀምበት በቅጥፈት የተሞላ ተቋም ማለት UNHCR

እንደሆነም ያስመሰከረው ጋዜጠኞች ላቀረቡላቸው ጥያቄ ኢትዮጵያዊያን እና ኤርትራዊያን ተጣልተው ነው ፖሊስ የመታቸው ሲሉ በመሀላችን ጸብ ለመጫር ሞከሩ ያለተሰካ ቅጥፈት ብለን አሁንም እኛ በህብረት ትግላችንን ቀጥለናል:: ለዚህ ደሞ ኤርታራዊያኑ የበተኑትን ጽሁፍ ማየት በቂ ነው::

"ሙተወከል..."የሚባል ሆስፒታል ነው ጊዜያዊ ህክምና የወሰድነው:: እኔ ካዛም አውጥተውኝ ሁለት ቀን ቤት ተኝቻለሁ:: በሁዋላ ግን ሳጣራ ለሆስፒታሉ ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሎት ሁሉን ነገር አዘጋጅተው ድብደባ ማድረጋቸውን ሰማሁ:: እንዲህ ነው የስደተኛ መርጃ ቢሮ ማለት ... ቀደሞ ሆስፒታል አዘጋጅቶ ያሚያስደበድብ:: በወቅቱ በደረሰብኝ የጤና ችግር ምንክያት ሁሉን ነገር ለመታዘብ እና ለማየት ባለመቻሌ ጉዳት የደረሰባቸውን ቃለ-ምልልስ ለማድረግ ተገደድኩ:: በዚህ አጋጣሚ የተሰባሰቡ ማስረጃዎች አሉ ጉዳት የደረሰባቸውንም ሰዎች አድራሻ ለሚፈልግ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ::


እንገቱን የተመታው ኡሰማን አብዳ

መጀመሪያ ያናገርኩት ኡስማን አብዳ ይባላል:: አንገቱ ላይ ነው ጉዳት የደረሰበት:: ሲናገር ቢቸግረውም እነሆ:-

**ጥያቄ:-** የእሁድ እለቱን ጭፍጨፋ እንዴት ታስታውሰዋለህ? እንደትስ ነው ጉዳት የደረሰብህ?

**ኡስማን:-** እኔ ታወቃለህ ከዚህ በፊትም መፍትሄ ይሰጠኝ ብዬ እዚሁ ተቀምጬ ነበር:: መፍትሄ የሰጡኝ ግን በዱላ ነው። በዛ ድብደባ ሚስቴ የ5ወር ጽንስ አስወርዳለች:: አሁንም እዚህ ካለው ቢሮ መፍትሄ ጠብቀን ሳይሆን ውጭ ያሉ ወገኖች ... ለነፍሳቸው ያደሩ ሰዎች መፍትሄ ይስጡን ብለን ነበር:: ግን ምን ያደርጋል:: በጥይት ቆሉን:: ይሄው እንደምታየው አንገቴ ላይ ተመትቼ ቆስያለሁ:: ልጆቼን ይዤ ነው UNHCR በር ላይ የወደኩት:: በረብሻው ሰዓት ልጄን ፖሊሱ መታው። የ4 አመት ህጻን ሲመታብኝ አትመታውም ብዬ ተከላለልኩ:: በዚህን ሰዓት በዱላ ሲማታኝ ወደኩ:: ዞረብኝ ... ጥሎኝ ጥቂት እንደተራመደ ከየት የተተኮሰ እንደሆነ ያላየሁት ጥይት መቶኛል ለካ ወደኩ:: ህይወቴን ይታደግልኛል ያልኩት UNHCR ህይወቴን ሊያጠፉት ታጥቆ ተነሳ .... /እንባ ስለተናነቀው ከዚህ በላይ ላወራው አለፈለኩም:: ሰለሞን ደሞ እንዲህ አጫዎተኝ:-

**ጥያቄ:-** እንዴት ነው ጉዳቱ? ሀኪሞች ምን አሉህ?

**ሰለሞን:-** አስለቃሽ ጋዙን ሲተኩሱ ጫፉ ላይ ያለችው ውልብልቢት ነገር ናት እግሬን ቆርጣ የሄደችው:: የደረሰብኝ ጉዳት እንደምታየው ከባድ ነው አጥንቴ ተሰብሯል:: ይሄ ሆነ መጨረሻችን:: አለም ይፍረደን.....

ቀጣይ ጥያቄ ያቀረብኩለት በድብደባ ወቅት በፖሊስ ዱላ ተጎድቶ ሙተወከል ሆስፒታል ታክሞ የወጣ ነው:: አብዱራዛቅ ይባላል::

**ጥያቄ:-** ምንህን ነው የተመታኸው?

**አብዱራዛቅ:-** ያሳፍራል!!! ስወድቅ እንደተንደረደረ ብልቴ ላይ በርግጫ መታኝ:: ስንፈራፈር በዱላው አናቴን መታኝ::

**ጥያቄ:-** አሁን እንዴት ነህ?

**አብዱራዛቅ:-** አሁን ደህና ነኝ ማለት አልችልም:: የተሻላ ህክምና ያስፈልገኛል:: እንደምታውቀው ደሞ UNHCR ቢሮውን ዘግቷል:: በእኛ አይደለም የተደበደቡት ለማለት የመን ውስጥ ባለው ጦርነት ምንክያን ቢሮው ስራ አቋርጧል ብለው ለጥፈዋል:: ዛሬ እኛ ስንደበደብ ነው የየመን ጦርነት የሚታያቸው? ... መቼ የተሻለ ህክምና እንደማገኝ አላውቅም::

ያናገርኳቸው ብዙ ቢሆኑም ሁሉም ተመሳሳይ ችግር እና አስተያየት ነው ያላቸው:: ሞት አድፍጦ እየለቀመን ሳለ በይፋ UNHCR ሲያስገድለን ምን ማለት ይቻላል? ሞት ይደንግጥ .. በ UNHCR በር ላይ ያለ ስደተኛ ግራ ቀኙን እየረገፈ ነው:: ሀገሪቷ ላይ መንግስት ይለወጥ ብለው ከ5 ወር በላይ ለተቃውሞ ሲቀመጡ ዝም መባላቸው እና ምስኪን ሀገሩ ያልሆነ የፖለቲካ ጥያቄ ያላነገበ ስደተኛ መፍትሄ ይሰጠኝ ብሎ ቢቀመጥ መደብደቡ ምን ያሳያል?የሀገሪቱ መንግስት አቋም አለመሆኑን ስደተኛውን UNHCR መበደሉን አያሳይም?

የተቻለኝን መረጃ አያይዣለሁ::